# መልክአ ኢየሱስ

ሰላም ለዝክረ ስምከ ስመ መሐላ ዘኢይሔሱ፣ ዘአንበረ ቅድመ እግዚአብሔር በአትሮንሱ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዳዊት ባሕርየ ከርሡ፣ አክሊለ ስምከ እንዘ ይትቄጸል በርእሱ፣ አህጉረ ፀር ወረሰ ኢያሱ::

ለማይታበለውና ለማይለወጠው ስም አጠራርህ ሰላምታ ይገባል:: አስቀድሞ በእግዚአብሔር ኅሊና የነበረ ነውና :: የዳዊትን ባሕርይ ባሕርይ ያደረግህ የስምህን ዘውድ በራሱ በመቀዳጀት ጠላቶቹን ድል አድርጐ መልካሚቱን ሀገር ወረሰ::

ሰላም ለሥዕርተ ርእስከ ዘሥሙር አብቋሉ፣ ወጽፉቅ ጥቀ ለአርዘ ሊባኖስ አምሳለ ቈጽሉ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናት ዘላዕለ ኵሉ፣ ይጽሐፍ በልሳንየ ለውዳሴከ ፊደሉ፣ ኢይትኃደግ ዲበ ምድር ንባቡ ወቃሉ::

አበቃቀሉ ለሚያምር ክቡር ለሆነው የራስ ፀጉርህ ሰላምታ ይገባል:: እንደ ለመለመ የሊባኖስ ዛፍ ራስ ክምር /ጽፍቅ/ ነውና:: የሁሉ በላይ የምትሆን የካህናት አለቃ አንተ ነህ:: ከቃሉና ከንባቡ አንዲት ቃል ስንኳ እንዳትጐድል የምስጋናህ መጽሐፍ ፊደል በአንደበቴ ሠሌዳ ላይ ተቀርጾ ይኑር::

ሰላም ለርእስከ በመንበረ ክሳድ ዘተሣረረ፣ እንዘ ማእሰ ሥጋ ይለብስ ወእንዘ ይትገለበብ ፀጕረ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ ቃልከ ነገረ፣ ይወርሱ በእንቲአከ ነዳያነ ዓለም ክብረ፣ ወቀደምትኒ ይከውኑ ድኅረ::

ሥጋን ለብሶ ፀጉርን ተጐናፅፎ የወርቅ ሸምበቆ የመሰለው ክሣድህን ዙፋን አድርጐ ለተቀመጠው ራስህ ሰላምታ ይገባል:: በማይታበለው ቃልህ እንደተነገረ ስለ አንተ ፍቀር በዚህ ዓለም የተቸገሩ ክብርን ይወርሳሉ:: ፊተኞች ግን ኋላኞች ይሆናሉ::

ሰላም ለገጽከ እምስነ ኦርያሬስ ስቡሕ ወፍሡሕ፣ ከመ ወርኀ ዘአሜ ገሐህ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ታቦተ ሕይወቱ ለኖኅ፣ ኅብአኒ እግዚኦ በውሳጤከ ስፉሕ፣ ማየ ኵነኔ አመ ዘንመ አይኅ::

ከፀሐይ ብርሃን ይልቅ እጅግ ለሚያበራው ፊትህ ሰላምታ ይገባል:: የደም ግባቱ ፀዳል ከጨረቃ ድምቀት ይበልጣልና::የኖህ የሕይወቱ ቃል ኪዳን ታቦት አንተ ነህ:: የኵነኔ ማየ አይህ በዘነመ ጊዜ ሰፊ በሆነ የቸርነትህ መጋረጃ ክልለኝ::

ሰላም ለቀናብርቲከ ከመ ክልኤ ክንፈ ኪሩብ፣ እለ ይጼልላ ወትረ አዕይንቲከ ዘርግብ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እደ መዝራዕቱ ለአብ፣ አስተጋብእ ውስተ ልብየ አቅማሐተ ኵሉ ጥበብ፣ ከመ ጽጌያተ ዘገዳም ያስተጋብእ ንኅብ::

እንደ ኪሩብ ክንፍ በሁለት አቅጣጫ ተንሰራፍተው አዕይንቲከ ዘርግብ ለተባሉ ዓይኖችህ ጌጥ ለሆኑ ቅንድቦችህ ሰላምታ ይገባል::የራቀውን የሚያቀርብበት የቀረበውን የሚያርቅበት የአብ ቀኝ ክንዱ ነህ:: ንብ የዱር አበባዎችን ቀስሞ ማር እንደሚያዘጋጅ የጥበባት ሁሉ ፍሬ የሚሆን ፈራሄ መለኮትን በልቡናየ አሳድርብኝ::

ሰላም ለአዕይንቲከ ከመ ምሉእ ምዕቃለ ማይ፣ እለ ይትረአያ ወትረ በመንበረ መጽሔት ርሱይ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ መስተሥርየ ኵሉ ጌጋይ፣ ንዝኅኒ እግዚኦ በአዛብከ ሠናይ፣ ወአፃዕድወኒ እምበረድ ጽሩይ::

ምሉዕ የሆነ እንደጠራ የምንጭ ውሃ ለሚሆኑ ዓይኖችህ ሰላምታ ይገባል:: ጌጥን በተጌጠ የአቀማመጥ መነፅር የሚታዩ ናቸውና::ኃጢአትን ሁሉ ይቅር የምትል ይቅር ባይ ነህና:: አቤቱ በይቅርታህ መነሳንስ እርጨኝ:: ከበረዶም ይልቅ እነፃ ዘንድ ከኃጢአት እጠበኝ::

ሰላም ለአዕዛኒከ ጽልዋተ እለ ከና፣ አምኃ ነገር ያብኣ ለመኰንነ ውስጥ ሕሊና፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘያዕቆብ ዓምደ ደመና፣ ምርሐኒ እግዚኦ ኀበ ዘይትፈቀድ ፍና፣ በዓመተ ርስዓን ወድካም ኢይርአይ ሙስና::

የፍጥረትህን ጥሪ ከመስማት ቸል ለማይሉ ጆሮዎችህ ሰላምታ ይገባል:: ኅሊናትን ሁሉ ለሚገዛ ወሳጣዊ ኅሊናህ ጉዳዩን ያስተላልፋሉና::ያዕቆብን በመንገድ የምትመራው የደመና ዓምድ ነህ:: በእርጅናዬና በድካሜ ሰዓት ከጥፋት ላይ እንዳልወድቅ አቤቱ በቀና ጐዳና ምራኝ::

ሰላም ለመላትሒከ እለ ይፈርያ አፈዋተ፣ ከመ ርኄ አፈው ዘይጼኑ ርትቀ ፍኖተ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እስመ አበ ነፍስየ አንተ፣ በሎሙ ለመላእክተ ተፈሥሑ ሊተ፣ ረከብክዎ ለወልድየ በከንቱ ዘሞተ::

መለኮታዊ ጸዳል /ወዘና/ ለረበበባቸው ጉንጮችህ ሰላምታ ይገባል:: እጅግ እሩቅ ጎዳና አልፈው ለሚሸቱ ሽቶዎች መመንጫ ናቸውና::የነፍስና የሥጋ ፈጣሪዬ እንደመሆንህ በከንቱ የጠፋውን ልጄን በደሜ ዋጅቼ አግኝቼዋለሁና:: እናንት የመላእክት ነገዶች ሁሉ ደስ ይበላችሁ በላቸው::

ሰላም ለአዕናፊከ መሳክወ ጼና ወአናቅጽ፣ እለ ውዱዳት እማንቱ ማእከለ ክልኤ አብያጽ፣ መልአከ ሕይወትየ ክርስቶስ አስተርእየኒ በገጽ፣ ናሁ ተመስጥኩ በጣዕመ መስቀልከ ዕፅ፣ ወተነደፍኩ በፍቅርከ ሐጽ::

የሽቱ መፍለቂያ ለሆኑ አፍንጮችህ ሰላምታ ይገባል:: እነርሱም የተማመኑ የሁለት ባልጆሮች አምሳል ናቸው:: የሕይወቴ ጌታ አንተ ስለሆንክ ገጽታህ ከገጽታዬ አይለይ:: እነሆ በመስቀል ላይ በፈሰሰው ደምህ ጣዕም ረክቼ:: ማኅየዊ በሚሆን ፍቅርህ ቀስት ተነድፌያለሁና::

ሰላም ለከናፍሪከ ሙኃዛተ ክርቤ ሐዋዝ፣ እምጽጌ ገዳማት ኵሉን ዘጼናሆን ምሉዝ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በግዐ ይስሐቅ እኁዝ፣ ይትከዐው ውስተ አፉየ ከመ አዜባዊ ውኂዝ፣ ነቅዐ ገቦከ በኵናት ርጉዝ::

እጅግ ያማረ የከርቤ መፍሰሻ ለሆኑ ከንፈሮችህ ሰላምታ ይገባል:: መዓዛቸው ከሚጣፈጥ አበባዎች የበለጠ መዓዛ ጣዕም አለውና::የይስሐቅን ሞት በሞትህ ለመለወጥ ከላይ በዕፀ ሳቤቅ ተይዘህ የቀረብህ ንጹህ በግ ነህ:: ሐራዊ ጐንህን በጦር ወግቶ ያፈሰሰውን ትኩስ ውሃ እንደ አዜብ የምንጭ ውሃ ተጕንጭቼው በኃጢት ፍትወቷ የተቃጠለውን ልቤን ቀዝቀዝ ያድርገው::

ሰላም ለአፉከ ለዮሐንስ ዘሰዐሞ፣ ንጽሐ ሕሊናሁ ወልቡ ለዓይነ ፍትወትከ ሰበ አደሞ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ መፍቀሬ የዋሓት እምተቀይሞ፣ ጸግወኒ ማዕዖ አፍ እንተ ይእቲ አርምሞ፣ ለትዕግሥትከ ከመ አእምር አቅሞ::

ዮሐንስን ለሳመ መለኮታዊ አፍህ ሰላምታ ይገባል:: የልቡናው ንጽሕና በፊትህ ተወዳጅነትን አግኝቷልና:: ቅያሜ ባንተ ዘንድ ቦታ የለውም ቸርነት ግን የባሕርይህ ነው:: ስለዚህ የትዕግሥትህን መጠን /ጥቅም/ አውቅ ዘንድ አፊም ክፉ ከመናገር ይቆጠብ ዘንድ የዝምታ ቁልፍ ስጠኝ::

ሰላም ለአስናኒከ አያተ አዕናቊ እለ ተሰክዓ፣ በፈትለ ሥጋ ወደም እስከ ሥረዊሆን ጸንዐ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘተሰመይከ ምሥዋዐ፣ ክርሥየ ርኅበ እግዚኦ ወውሳጤ ጕርዔየ ጸምአ፣ እንበለ ከኑኔ ሀበኒ ሥጋከ መብልዐ::

በደምህ በሥጋ በተዋሐደ /በተስማማ/ ፈትል ሥራቸው ፀንቶ እንደዕንቁ ሠንጠረዥ ለተደረደሀሩት ጥርሶችህ ሰላምታ ይገባል:: በአባትህ ፊት የተወደደ መሥዋዕት ሆነህ ስለቀረብህ አቤቱ ሆዴ ተርቧል ጕሮሮዬም ከጥማት ብዘት የተነሣ ነቅቷልና /ተንጣጥቷልና/ ያለምንም ወቀሳ ሥጋህን ለመብላት ደምህንም ለመጠጣት ስጠኝ::

ሰላም ለልሳንከ በደብረ ታቦር ዘአልኖሰሰ፣ ለብርሃን ዓቢይ እስከ ጽላሎቱ ተሐውሰ፣ ነበልባለ እሳት ክርስቶስ ዘተዋሐድከ ጳጦሰ፣ በዋዕየ ፍቅርከ ከመ ሥርወ አዕዋም የብሰ፣ ውሳጤ ሕሊናየ ነደ ወልብየ ጤሰ::

በታቦር ተራራ ምሥጢረ መለኮትህን ለመግለጽ ለተንቀሳቀሰው አንደበትህ ሰላምታ ይገባል:: ከድምፅህ ግርማ የተነሣ የታላቁ ብርሃን ዓመድ ተነዋውጧልና::ያለማቃጠል የሲናን ዕፅ የተዋሐድህ የእሳት ነበልባል አንተ ነህ:: የዛፎች ግንድ በእሳት እንደሚቃጠል ሁሉ በፍቅርህ ነበልባል ልቡናዬ ጤሰ ውስጣዊ ኅሊናዬም ነደደ::

ሰላም ለቃልከ እማእሰሪሁ ዘፈትሖ፣ ለፍቁር አልአዛር ኃይለ ሥልጣነ ሞት ድኅረ ሞቅሖ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሠ ሰላም ወተራኅርኆ፣ አባ ወአቡየ እሴብሐከ ሰብሖ፣ ለአንቀጽከ ጸግወኒ መርኆ::

ቸር ማኅየዊ ለሚሆን ቃልህ ሰላምታ ይገባል:: የሞትን ሥልጣን ሽሮ አልዓዛርን ከመቃብር አስነሥቷልና::የሰላምና የቸርነት ንጉሥ ነህና አባት ሆይ የቸርነትህን በር ትከፍትልኝ ዘንድ ልባዊ የሆነ ፍጹም ምስጋናን አቀርብልሃለሁ::

ሰላም ለእስትንፋስከ እስትንፋሰ ላህብ ምዉቅ፣ ጊዜ ፍና ሠርከ ዘነፍኅ ገነተ ኅሩያን ደቂቅ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ጠፈረ ሃይማኖት ወጽድቅ፣ ይትወሀውሁ ከዋክብት በአየርከ ምጡቅ፣ ወያንበሰብሱ ደመናት በዐረብ ወሠርቅ::

በአዳም ፊት ላይ እፍ ላለ እስትንፋስህ ሰላምታ ይገባል:: ደጋጐች ልጆች በሆኑ የመናፈሻ ቦታ ላይ ጥሩ አየርን ያመጣልና:: የጽድቅና የሃይማኖት ጠፈር ነህ:: ስለዚህም ምጡቅ በሆነ አየር ላይ ከዋክብት ያንጸባርቃሉ:: ደመናትም ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ይመላለሳሉ::

ሰላም ለጕርዔከ በጽምአ ፍቅረ ሰብእ ሐማሚ፣ እስከ ስቴ ሐሞት ጥዕመ ወዘወይነ ትፍሥሕት ከራሚ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ መምህረ ጳውሎስ ዘብንያሚ፣ አመ ነሥአ ማኅተመ ጸጋ እንዘ ስመከ ይሰሚ፣ አልቦ አይሁድ ወአልቦ አረሚ::

ለሰው ፍቅር ሲል ለተጠማ ጕሮሮህ ሰላምታ ይገባል:: መራራ ሐሞትን እስከ መጠጣት ደርሷልና:: የብንያማዊ የጳውሎስ መምህር ነህ:: ስለዚህ በስምህ አምኖ የመታወቂያ ማኅተም ካርድ የያዘ ከክሐዲነትና ከአረማዊነት ነጻ የወጣ ነው::

ሰላም ለክሳድከ ግብረ መንፈስ ቅዱስ ኬኒያ፣ አዳም ስና ወመንክር ላህያ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ነቢይ ወሐዋርያ፣ አመ ወጽአ ስሙዓቲከ በአድያመ ኵሉ ሶርያ፣ ብፁዓት አዕይንት ኪያከ ዘርእያ።

በመንፈስ ቅዱስ ግብር ለተከናወነው የአንገትህ ሥራ ሰላምታ ይገባል። አቋሙ ደም ግባቱ እጅግ አስደቂ ነውና። ነቢይም ሐዋርያም ነህ አኮን። አምላካዊ ተአምራቶችህ በሶሪያ አወራጃ በተገለጹ ጊዜ አንተን ያዩ ዓይኖች ንዑዳን ክቡራን ናቸው።

ሰላም ለመትከፍትከ ከመ ልብሰ ክህነት ሎግዮ፣ ጊዜ ፀአተ ፍትሕ ዘፆረ አርዑተ መስቀል በቀራንዮ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በግዐ መድኃኒት ወአስተሥርዮ፣ አስተዳሎከ ለርእስከ ውስተ ዐፀደ ግፍዕ ተርእዮ፣ ወኵሎ በዘይደሉ አቅደምከ ሐልዮ።

በቀራንዮ አደባባይ ፍርድን ለመቀበል በወጣ ጊዜ ሎግዮ እንደሚባል ልብሰ ተክህኖ መስቀልን ለተሸከሙ ትከሻህ ሰላምታ ይገባል።ኃጢአትህን የሚያስተሰርይ በግዓ መሠዋዕት አንተ ነህ። ስለኛ መከራን ለመቀበል በግፍ አደባባይ መታየት ፈቃድህ ሆነ። ይህ ሁሉ እንዲሆን አንተ አስቀድመህ ያዘጋጀኸው ነውና።

ሰላም ለዘባንከ እመለኮቱ ዘኢተዐርቀ፣ እንዘ በአፍአሁ ይትዌከፍ ጥብጣቤ ሕማማት መጽዕቀ፣ ጕንደ ሐረገ ወይን ክርስቶስ እንተ ትፀውር አዕፁቀ፣ በቤተ ከብካብ ጊዜ ትገብር ምርፋቀ፣ ለአስካልከ ረሰየኒ ዝቀ።

በብዙ መቶ ሺ የሚቆጠር ግርፋትን ለተቀበለ ዘባንህ ሰላምታ ይገባል። ይህም ሁሉ ሲሆን መለኮቱ ከሱ አልተለየምና።ልምላሜንና የፍሬ ዘለላን የተሸከመህ የወይን ሐረግ ጉንድ ነህ። ለወዳጅህ የሠርግ ቤትን ባዘጋጀህ ጊዜ እኔን የማዕድ አስተናባሪ /የወይን ማጣሪያ/ አድርገኝ።

ሰላም ለእንግድዓከ ቀላየ ልቡና ወአእምሮ፣ በሐመረ ፍትወት ወጻሕቅ ልበ ጠቢባን ዘኢሰፈሮ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ኄሩት ወተፋቅሮ፣ ሰበ ይገሥሥ ሕሊናየ ለመንዲልከ ዘፈሮ፣ ነቅዐ ኃጢአትየ ለገብርከ አምድሩ ይሠር።

የዕውቀትና የማስተዋል መገኛ ለሆነ ደረትህ ሰላምተ ይገባል። የጥበበኞች መራቀቅና መፈላሰፍ ተመራምሮ ሊደረስበት በፍጹም አይችልምና። የፍቀርና የቸርነት ባለቤት እንደመሆንህ መጠን የመጐናጸፊያህን ዘርፍ እደ ኅሊናየ በዳሰሰ ጊዜ የኔ ያገልጋይህ ኃጢአት ከሥሩ ተመንግሎ ይውደቅ።

ሰላም ለሕፅንከ ምርፋቀ በረከት ወሣህል፣ ዘአስመከ ቦቱ ወልደ ዘብዴዎስ ድንግል፣ኢየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖትየ ወንጌል፣ ከመ ዕፀ ሐምል ስፍሕተ አዕፁቅ ወቈጽል፣ ብዙኃተ አዕዋፈ አጽልሎተ ትክል።

የበረከትና የይቅርታ ማረፊያ ወደብ ለሆነ ሕፅንህ ሰላምታ ይገባል። ይኸውም የዘብዴዎስ ልጅ ዮሐንስ ያረፈበት ነው። የማምንብህ ቅድስ ወንጌል ነህ አጽቆቿ የበዙ ቅጠሎቿ ሰፋፊ የሆኑ ዛፍ ብዙ አዕዋፍን ለመጠለል እንደምትችል እኔም በክንፈ ረድኤተህ ሥር ልጠለል።

ሰላም ለአእዳዊከ ጽቡረ እለ ገብራ፣ በምራቀ አፉከ ቅዱስ አዕይንተ ዕውር ይፍጥራ፣ ትምህርተ ኀቡአት ክርስቶስ ዘትትነገር እምጽርስፎራ፣ ነገሥታት በእንቲአከ ይገድፉ ጌራ፣ ወዕጠቆሙ ይፈትሑ ሐራ።

በደረቅ ንግባር ዓይንን ይፈጥሩ ዘንድ በተቀደሰው የአፍህ ምራቅ ጭቃን ለለወሱ እጆች ሰላምታ ይገባል። በጽርስፎራ በሥጋ ወደሙ የምትነገር ትምህርተ ኅቡአት ነህ። ስለ አንተ ነገሥታት ዘውዳቸውን ያወርዳሉ ሠራዊቶቻቸውም ትጥቃቸውን ይፈታሉ።

ሰላም ለመዛርዒከ ከመ ቀስተ ብርት ጽኑዕ፣ ለመዛርዒከ ከመ ቀስተ ብርት ጽኑዕ፣ እለ ያነትዐ ፀረ አመ ዕለተ መንሱት ወጸብእ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ጠረጴዛየ ምሥዋዕ፣ አስትየኒ ማየ ሕይወት እመስቀልከ ጽዋዕ፣ ዘእንበሌሁ ኢይድኅን ሰብእ።

እንደጽኑ የብረት ቀስት ለሚጠነክሩ ወርቾችህ ሰላምታ ይገባል። በንብና በሽብር ቀን ጠላትን ያንበረክካሉና። መሥዋዕት የምሠዋብህ ጠረጴዛየ ነህ ከመስቀልህ ጽዋ ማየ ሕይወትን ከጠጣኝ። ያለ እርሱ ማንም ሊድን አይችልምና።

ሰላም ለኵርናዕከ ክቡድ አንበሳ፣ ዘቀጥቀጠ ኵሎ አርእስተ ስቡሐን እንስሳ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞገሰ ዳንኤል ነቢየ ሱሳ፣ ድኅረ ተፈጸመ ሱባዔ ሰንበታት ስሳ፣ በምጽአትከ ተኀትመ አበሳ።

የሰቡ እንስሳትን ራስ እንደሚቀጠቅጥ እንደ አንበሳ ኩርማ/ክርንህ/ ሰላምታ ይገባል። የነብዩ ዳንኤል ግርማ ሞገሱ አንተ ነህ። ጊዜው ሲደረስ ትንቢቱ ሲፈጸም ደቂቃ ሳታልፍ በመምጣትህ በደላችንን አጥፍተህ ኃጢአታችንን ደምሰስህ ጠላታችንን ድል አድርገህ ከባርነት ነፃ አወጣኸን።

ሰላም ለእመትከ መስፈርተ መዛርዕ ወእድ፣ እስከ ጽንፈ መስቀል በሐብል ዘሰሐብዎ አይሁድ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እምነ አእላፍ ውሉድ፣ ኅድፈኒ በጥበብከ እምተሰጥሞ ጌጋይ ክቡድ፣ ናሁ በላዕሌየ ተንሥአ ሞገድ።

የእርጅና የወርቾህ መመጠኛ ለሆነ ጠንካራ ክንድህ ሰላምታ ይገባል። እስከ ቀራንዮ ድረስ በገመድ አሥሮ ለመጐተት አይሁድን ብዙ ኃይል ጠይቋቸዋልና። ከአልፍ አእላፍ የተመረጥህ ነህ እነሆ ኃጢአት ማዕበል ሞገድ በላዬ ላይ ተነስቶብኛልና በበደል ባሕር ከመስጠም አድነህ በጥበብህ አሻግረኝ።

ሰላም ለእራኀከ መክፈልተ ሕማማት ሱቱፍ፣ ወቅንዋቲሁ እኤምኀ በአፍ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በላዕለ ቅዱሳን ዕሩፍ፣ ይፀነስ ውስተ ክርሥየ ዘርአ ቃልከ መጽሐፍ፣ ፀዳለ እምፀዳል ከመ ትፀንስ ያፍ::

ቅንዋትን በአኰቴት ተቀብሎ የሕመምህ ተሳታፊ ለሆነ መሐል እጅህ ሰላምታ ይገባል:: በቅዱሳንህ ሁሉ አድረህ የምትኖር ነህና ወፍ ብርሃንን ከብርሃን እንደምትፀንስ የቃልህ ዘርዐ መጽሐፍ በሆዴ ይሥረፅ::

ሰላም ለአፃብዒከ አፃብዐ አዳም ዘተኬነዋ፣ ወነቀለ ዐፅመ በእንተ ሕይወታ ለሔዋ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ አመ ተሰዐልከ እምድር ፄዋ፣ ለገነተ ጽድቅ ዘእደ ሱራፊ ዐጸዋ፣ ቤዛ ኃጥአን ኲሎሙ ደምከ አርኀዋ::

የሰው ዘር ሁሉ አባት የሚሆን አዳምንና ከጐኑም አንዲት አጥንት ነሥተው ሔዋንን ለፈጠሩ ጣቶችህ ሰላምታ ይገባል:: ከትንሣኤህ በኋላ በ፵ኛው ቀን ከምድር ወደ ሰማይ ባረግህ ጊዜ የኃጥአን ቤዛ የሆነ ደመ ማኅተምህ ሱራፌ የዘጋውን የገነት በር ከፈትልን::

ሰላም ለአጽፋረ እዴከ ዘኀበሪሆን ፀዐዳ፣ በምግባር ወግእዝ እለ ይትዋሐዳ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ምስፍና አባሉ ለይሁዳ፣ ለመንግሥትከ ሰፋኒት እንዘ ይትመሃለሉ ዐውዳ፣ ሰብአ ሰገል አወፈዩ ጋዳ::

ኅብራቸው ነጭ ለሆነ የእጅ ጥፍሮችህ ሰላምታ ይገባል:: እሊኸውም በሥራና በጠባይ ፍጹም አንድ ናቸው::ለይሁዳ የምስፍናው ደጀን ስለሆንህ ገዥ በሚሆን የመንግሥትህ አደባባይ ተሰብስበው ሰብአሰገል እጅ መንሻ አቀረቡልህ::

ሰላም ለገቦከ ዐዘቅተ ሥጋዌ ፍሉሕ፣ እንተ እምኔሁ ተውህበ ፈልፈለ ቅድሳት ወንጽሕ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘኢሳይያስ መካሕ፣ አመ አስተርአይከ በልብሰ ባሶር ቀይሕ፣ መልአከ ሞት ተሰጥመ በላህ::

ፍሉህ የሚፍለቀለቅ የሥጋዌ መፍለቂያ ለሆነ ጐንህ ሰላምታ ይገባል ይኸውም የቅድስናና የንጽሕ ምንጭ ነው::ነቢዩ ኢሳይያስ ስለ ነቢይነቱ እጅግ አድርጐ የሚመካብህ ነህ:: አምላኬ ሆይ መለኮትህን ከሥጋ ጋር አዋሕደህ በዚህ ዓለም በተገለጽህ ጊዜ መልአከ ሞት በልቅሶ ባሕር ሰጠመ::

ሰላም ለከርሥከ ዘኢትፌተን መዝገቡ፣ ሚ ዕመቁ ወሚ ራኀቡ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ለወንጌለ ንግሥከ በወርኀ ምግቡ፣ እለ ይነግዱ ዲበ ባሕር አስትአ በረከተ ወሀቡ፣ ወእለ የኀድሩ ዲበ የብስ አምኃ አቅረቡ::

ምን ይጠልቅ ምን ይስፋ ተብሎ ለማይመረመረው ሆድህ ሰላምታ ይገባል:: የሰው ኅሊና የመላእክት አእምሮ አስቦ ሊደርስበት አይችልምና::በወንጌል መንግሥትህ ወራት በባሕረ በመርከብ የሚመላለሱ ገጸ ረከትን ሰጡ:: በየብስም የሚኖሩ እጅ መንሻ አቀረቡ::

ሰላም ለልብከ ቅሩብ ኲልያት ምንታዌ፣ እንተ ያንስሐስሕ ቦቱ መንፈሰ ሕሊናከ ኀበ ህላዌ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹመ ትስብእት ወሥጋዌ፣ በቀለ በእንቲአከ አመ ትትፋታሕ ነነዌ፣ ውስተ መቅደስከ ረሰየኒ ሠርዌ::

መንታ ለሆኑ ኩልያቶችህ አቀረብ ለሚሆን ልብህ ሰላምታ ይገባል:: የኅሊናህ መንፈስ ወደ አነዋወሩ የሚመላለስበት ነውና::ሥጋን ከመለኮት ጋር ያዋሐድክ ፍጹም አምላክ ነህ:: ስለ አንተ በቀል ነነዌ በተፋረደች ጊዜ በመቅደስህ ውስጥ አለቃ አድርገኝ::

ሰላም ለሕሊናከ ወይሔሊ ሠናያተ፣ ለውሉደ ሰብእ ምሕረተ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘአሰሰልከ ጽልመተ፣ ላዕለ ኪሩቤል ነቢረከ ዘትሬኢ ቀላያተ፣ ስቡሕኒ ወልዑል አንተ::

የበጐ ነገር ምንጭ ለሆነ ኅሊናህ ሰላምታ ይገባል:: ለሰው ልጅ ሁሉ ቸርነትን ከማድረግ አይቆጠብምና:: ከዓለም ላይ ጭለማን ያስወገድህ እውነተኛ ብርሃን አንተ ነህ ከላይ በኪሩቤል ላይ ተቀምጠህ የውቅያኖስን ጥልቅነት ትመለከታለህ ስለዚህም ልዑልና የተመሰገንህ ነህ::

ሰላም ለኀንብርትከ ማእከለ ጠባይእ ዘተመልአከ፣ በኲሉ ቱስሕቱ እንዘ ይትሜሰል ማእከከ፣ መንግሥተ ሰማያት ክርስቶስ ከመ ዮሐንስ ሰበከ፣ በሐፍ ወበድካም እለ አሥመሩ ኪያከ፣ ዲናረ ሃይማኖት ነሚአሙ የአትዉ ሠርከ::

በባሕርያት መካከል ገዥ ለሆነ ሕንብርትህ ሰላምታ ይገባል:: ህልውናው እንደ ዕንቁ ፈርጥ ነውና:: ዮሐንስ እንዳስተማረ እንደተናገረ በድካማቸው በወዛቸው አንተን ያስደሰቱ ሁሉ የሃይማኖትን የወረቀ መዳሊያ ተሸልመው ወደማታ መንግሥተ ሰማያት ይገባሉ::

ሰላም ለሐቌከ እንዘበ ልዕልና፣ ከመ ገብር ድኩም ዘቀነተ ሐብለ ትህትና፣ ኅብስተ ሕይወቶሙ ክርስቶስ ለእለ ይነሥኡ ስመ ክርስትና፣ አኮአ ኅብስተ እስራኤል መና፣ ዘዕሜተ ሞት ፈደየ በሲና::

መላእክትን የእሳት ዝናር የሚያስታጥቃቸው ልዕልና እያለው እንደ ደካማ ባሪያ የትሕትና /የመዋረድ/ ዝናር ለታጠቀ ወገብህ ሰላምታ ይገባል:: ስመ ክርስትናን ለተቀበሉ ሁሉ የሕይወት እንጀራቸው ነህ:: ይኸውም እስራኤል በደላቸው ምክንያት ሞትን እንዳስከተለባቸው እንደ ሲና በረሃ ያለ

ኅብስተ መና ያይደለ ለዓለሙ ሁሉ ሕይወትን የሚያድል የሕይወት ኅበስት ነው እንጂ::

ሰላም ለአቍያጺከ አዕማድ ያቁም ወበለዝ፣ እለ ይጸውራ ቦቶን መልክዐተ ኵሉ ትእዛዝ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ምጽላለ ሕይወትየ አርዝ፣ ተበአሶ በጽላሎትከ ለአርዌ ዐመፃ ወሕምዝ፣ ኢይሳኅነኒ ለገብርከ ዳግመ አምዝ::

እንደ ብረት ምሰሶ ለሆኑ አቁያጽህ ሰላምታ ይገባል:: መለኮት ለተዋሐደው አካለ ቆምህ ተሸካሚ ዓምድ ሆነዋልና:: የሕይወት የጥላ ዛፍ አንተ ስለሆንክ እኔን ባሪያህን ዳግመኛ እንዳይጠላኝ የመርዝና የተንኰል ወገን የሚሆን ጠላቴን በጥላህ ውጋልኝ::

ሰላም ለአብራኪከ እለ አውተራ ስግደተ፣ እንዘ የዐርጋ ላዕለ ወእንዘ ይወርዳ ታሕተ፣ ጊዜ ተቀባእከ ክርስቶስ ለአልባስጥሮስ ዕፍረተ፣ ገብርከሰ እምፈተውኩ አሜሃ ዕለተ፣ ማርያም ትኩነኒ እኅተ::

የምድር ነገሥታት የሰማይ መላእክት ከሚሰግዱልህ ከላይ ወደታች ከታች ወደ ላይ በማለት ስግደትን ሳዘወተሩ ጉልበቶችህ ሰላምታ ይገባል:: ለመታሰቢያህ የሚሆን የአልባስጥሮስ ሽቱ በተቀባህ ጊዜ በዚያን ቀን ወይም ያን ጊዜ ማርያም እህት በሆነችኝ በወደድሁ ነበር::

ሰላም ለአእጋሪከ እለ ጠብዐ ለቀዊም፣ ቅድመ ጲላጦስ ፈታሒ መስፍነ ይሁዳ ወሮም፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘትማልም ወዮም፣ ኀበ ወረደ ወነጠበ ዝናመ አእጋሪከ ደም፣ለቋስቀልከ በሰጊድ ሰላም::

መላእክት በመንቀጥቀጥና በመፍራት ከፊታቸው ለሚቆሙት በሮምና በይሁዳ መስፍን ፊት ለቆሙ እግሮችህ ሰላምታ ይገባል::የትላንቱም የዛሬውም የነገውም አለኝ ታዬ አንተ ስለሆንክ:: በዕለተ ዓርብ የእግርህ ደም እንደጐርፍ ውሃ በወረደ ጊዜ ለተሰቀልክበት መስቀልህ ሰላም እያልኩ እጅ እነሣለሁ::

ሰላም ለሰኰናከ እንተ ያስተጋብእ ኵሎ፣ ኀበ ኀደገ ወቀጽዐ ውስተ ሰሌዳ ኰኵሕ ሥዕሎ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመልአከ ዓለም ወትትቤቀሎ፣ ስብሐቲከ እርአይ እግዚኦ እቅድመ ዓለማት ዘሀሎ፣ መንጦላዕተ ዐይንየ ቅላዕ ወአብርኅ ጸዳሎ::

ለአባላትህ ሁሉ ሥርወ ጉንድ ለሆነው ተረከዝህ ሰላምታ ይገባል:: በኰኩህ ሠሌዳ አምሣል ሁሉን ቀርፆ አቀናብሮ ይዟልና:: የዚህን ዓለም ገዥ /ሞትን/ የምትበቀለው አንተ ነህ:: አቤቱ ዓለም ሳይፈጠረ የነበረውን ክብርህን አይ ዘንድ የዓይኔን መጋረጃ ግለጥ ፀዳሉንም አበራ::

ሰላም ለመከየድከ አሐዱ አሐዱ፣ ውስተ ቤተ መቅደስ ለምህሮ እለ ገይሰ ለመዱ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመዓዛ ፍቅርከ ዕቍረ ናርዱ፣ አኃዊየከ ሰማዕታት ቈላተ ሕማማት ወረዱ፣ ወጻድቃኒከ ገዳማተ ጎዱ::

የእግዚአብሐርን መንግሥት ለማስተማረ ወደ ቤተ መቅደስ ለሚገሠግሱ ለያንዳንዱ የእግሮችህ አረማመድ ሰላምታ ይገባል::ከናርዱ ሽታ በሚበልጠው የፍቅረህ መዓዛ ጣዕም ወንድሞችህ ሰማዕታት ወደ ሥቃይ በረሃ ወረዱ:: ወዳጆችህ ጻድቃንም ወደተጋድሎ ዱር ተሰደዱ::

ሰላም ለአጸብዒከ እምጕንደ ክልኤ አእጋር፣ እለ አሕመልመላ ደርገ አርአያ አዕፁቀ ዐሥር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር፣ በዘባነ ባሕር ከመ ትትለሀይ ሐመር፣መንክር ተላህያ በዘለከ ፍቅር::

ከወይን ሐረግ አዕፅቅ በልምላሜ እንደበቀሉ ከሁለቱ እግሮችህ በዓሥር አቅጣጫ ለበቀሉ ጣቶችህ ሰላምታ ይገባል::ተቀዳሚ ተከታይ የሌለህ አንድ የግዚአብሔር ልጅ አንተ ነህ መርከብ በባሕር ላይ እየተንሣፈፈች እንደደትይዝ የመወደድህም ለዛ እንዲሁ ድንቅ ናት::

ሰላም ለአጽፋረ እግርከ በደመ ቅንዋት እለ ተጠምዓ፣ እስከ ዕዕዳዊሆን ለብሰ ልብስተ ጠባይዕ ካልአ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘተሰቀልከ በአፍአ፣ እንዘ እዜኑ ኂሩተከ ወእከውን ስመዐ፣ መምህረ ረሰይኩከ ረስየኒ ረድአ::

ቅንዋት ባፈሰሱት ደምህ ለተቸነከሩ የእግር ጥፍሮችህ ሰላምታ ይገባል:: ከንጻታቸው የተነሣ ልዩ ባሕርያት አላቸውና::ለሰው ልጅ ደህንነት ስትል በቀራንዮ አደባባይ የተሰቀልህ አንተ ነህ:: ስለዚህ ቸርነትህን እየተናገርኩ ምስክር እሆን ዘንድ እኔ መምህሬ እንዳደረግሁህ አንተም ደቀመዝሙርህ አድርገኝ::

ሰላም ለቆምከ ሐመልማለ ቀይሕ ሥጋ፣ ክርስቶስ ቀዳሜ ጸጋ፣ ናሁ ሰፈነት ወሰፈፈት እንበለ ንትጋ፣ ለባሕረ ሣህልከ ዘኢይነጽፍ ፈለጋ፣ ውስተ ሕሊናየ አስተጋብእ አይጋ::

በቀይሐ ሥጋ ለለመለመ ሥነ ቆምህ ሰላምታ ይገባል:: ሕያው ማኅየዊ የምትሆን አንተ አስቀድሞ ለኛ ተሰጥተሃልና::እነሆ የቸርነትህ ባሕር በወንዟ መላች ተሾመች:: የለመጉደልም በምልዓት ትኖራለችና:: የመፍለቂያዋን ምንጭ በልቤ ውስጥ አድርግ::

ሰላም ለመልክዕክ መልክዐ ክቡር አምላክ፣ እለ ይቴሐታ ሎቱ አርእስተ ሰኮና ወብርክ፣ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያነ መልአክ፣, ይትመላኅ አምሕሊናየ በተግሥፅከ፣ ቡሩክ ሕጠተ ደዌ ዘበቈለ ሦክ።

ፍጥረት ሁሉ ጉልበት በመዋረድ የሚሰግዱለት ክቡር ለሚሆን አምላካዊ መልክህ ሰላምታ ይገባል።መምህራችንም ገዛችንም አንተ ነህና ከክፋት ወደ በጎነት የሚመልስ በጎ ተግሣፅን በልቤ ላይ የበቀለውን ሶክ ኃጢአት ይንቀልልኝ ።

ሰላም ለፀአተ ነፍስከ ኀይለ ሥልጣነ ሞት ዘቀነየ፣ ጽዋዐ ፓሲካ ምሉእ ድኅረ ሰለጥከ ሰትየ፣ ጥዑመ ከናፍር ክርስቶስ እንተ ትነብር ሰደየ፣ ምባት ወበሕይወት አምኅፀንኩ ነፍስየ፣ ውስተ እዴከ ዘገብረ ሰማየ።

በገዛ ሥልጣንህ ነፍስህን በመስጠት ጽዋ ሞትን ጠጥተህ ከጨለትክ በኋላ ሥልጣነ ሞትን ለደመሰሰ ፀአተ ነፍስህ ሰላምታ ይገባል።
የመልካም አነጋገር ለዛ ለከንፈርህ ልዩ ውበት ይሰጠዋል። ሰማይና ምድርን ለፈጠረ መለኮታዊ እጅህ በሞቴም በሕይወቴም ነፍሴን /ሰውቴን/ አደራ እሰጣለሁ።

ሰላም ለበድነ ሥጋከ እመለኮቱ ዘኢተፈልጠ፣ ለሰዓት አሐቲ ከመ ቅጽበተ ዐይን ኅዳጠ፣ መዝገበ ባሕርይ ክርስቶስ ዘኢተአምር ተውላጠ፣ አኮ ዘሐይቅ ጽጌረዳ ወዘባሕር ሰግላጠ፣ባሕቱ ሃይማኖትየ እሁበከ ሜጠ።

ለዓይን ጥቅሻ ወይም ቅጽበት ለማትሞላ ሰዓት ስንኳ ከመለኮቱ ላልተለየ በድነ ሥጋህ ሰላምታ ይገባል። ኀልፈት ውላጤ የሌለብህ የበሕርይ አምላክ ነህ ስለዚህ ዋጋን ለማግኘ ት የሐይቅን ዳርቻ ጽጌ ረዳ ወይም የባሕርን ሸቱ የማቀርብልህ አደለም። ፍጹም የሆነ ልባዊ ሃይማኖቱን ነው እንጂ።

ሰላም ለግንዘተ ሥጋከ በአፈወ ከርቤ ሕውስ፣ ወበልብሰ ገርዜን ንጹሕ ዘኀበሪሆን ቢሶስ፣ መርዓዊ ሥርግወ አመ ትመጽእ ክርስቶስ፣ ዐሥረኒ ለቀበላከ በማኅቶተ ምግባር ውዱስ፣ ከመ ደናግል ጠባባት ዘኍልቆን ኅምስ።

ከልዩ ልዩ ዓይነት ቅመም የተቀመመ ሽቶና ከርቤ በተቀላቀለበት እንዲሁም ኅብሩ አረንጓዴ በሚመስል ድርብ በፍታ ለተገነዘ ሥጋህ ሰላምታ ይገባል።በተሸለመ የሙሽራ አምሣል ተመስለህ ድንገት በመጣህ ጊዜ ብልሆችና ዐዋቂዎች እንደሆኑት አምስቱ ደናግል ብሩህ የሆነ የምግባር ፋና መብራት አብርቼ እቀበልህ ዘንድ ቅጠረኝ /አድመኝ/።

ሰላም ለመቃብሪከ መካነ ምሥጢር ጎልጎታ፣ ቀዳሚ አዳም ዘኢተቀብረ በውስቴታ፣ኢየሱስ ክርስቶስ በረከተ ኤልያስ ዘሰራፕታ፣ ሣህልከ ወምሕረትከ ይመግቡኒ በፆታ፣ከመ ሐገፋ ወሥሙር ወልታ።

የቀደመ አዳምና ልጆቹ ያልተቀበሩበት ምሥጢራዊ ለሆነች በጎልጎታ ለምትገኘው መካነ መቃበርህ ሰላምታ ይገባል። ለኤልያስ በስራኘታ በረከትን የሰጠኸው ወሀቤ ምረከት አንተ ነህና ይቅርታህና ቸርነትህ ሁሉም በየወገናቸው ጋሻ መከታ ሆነው ከሚሠነዘሩብኝ ሁሉ ይጠብቁኝ /ከላላ ይሁኑኝ/።

ሰላም ለትንሣኤከ አምድኅረ ዕለታት ክልኤ፣ ዐቀብተ መቃብር አፅላፍ እንበለ ይስምዑ ቀርነ ጽምዔ፣ ወበእንተዝ ይብሉከ ክርስቶስ በኵረ ትንሣኤ፣ ተአመንኩ ወተወከልኩ ቅድመ ገጸ ኵሉ ጉባኤ፣ ኪያከ አበ ወኪያከ ረዳኤ።

ክቡር የሚሆን የመቃብርህ ጠባቂዎች ከድንጋጼ የተነሣ የትንሣኤህ ግርማ የገለባበጣቸው በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይተህ ለተነሣኸው ትንሣኤህ ሰላምታ ይገባል። ስለዚህም ለሙታን ሁሉ ጐዳና ጠርገሃልና በጉባኤ ሁሉ ፊት አንተን ረዳት አደረጋለሁ። እንደ አባትም አድርጌ እመካብሃለሁ።

ሰላም ለትንሣኤከ እንተ ተጠየቀ ቦቱ፣ ዜና ትንሣኤሆሙ በክብር ለቅዱሳን ዘሞቱ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዳዊት ቀርነ መንግሥቱ፣ በዓለ ትንሣኤ ፋሲካነ ዝንቱ፣ እስመ ሥርዓቱ ለእስራኤል ውእቱ።

ስለፍጹም ሃይማኖት በክብር ለሞቱ ቅዱሳን ሁሉ የትንሣኤያቸው መረጃ /መተማመኛ/ ለሆነው ትንሣኤህ ሰላምታ ይገባል። ለዳዊት የመንግሥቱ መለከት አዋጅ ነጋሪ ነህ። ስለዚህ የትንሣኤህ በዓል የደስታ በዓላችን ነው። ሥርዓተ ሕጉ የእሥራኤል ሥርዓት ነውና።

ሰላም ለዕርገትከ ዘኢይትረከብ መጠኑ፣ ወለንብረትከ ሰላም ለአቡከ ውስተ የማኑ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እለ ኪያከ ተአመኑ፣ ቅዱሳነ ዘእምኀቤከ ወንጹሐነ ያኩኑ፣ ጳራቅሊጦስ መንፈስከ ፈኑ።

ምጥቀቱ ለማይመረመር ዕርገትህ ሰላምታ ይገባል። በአባትህ ቀኝ ለመቀመጥህም ክብር ይገባል።በአንተ ለሚያምንና ለሚተማመኑ ሁሉ የተቀደሱና ንጹህ ይሆኑ ዘንድ እንደ በረዶ የሚያነፃ እንደ ውሃ የሚያጠራ ካንተ ዘንድ የሚገኝ መንፈስህን ላክላቸው።

ሰላም እብል ለምጽአትከ ከዋላ፣ በደመና ሰማይ ብርሀት እንተ ትፀድል እምስነ ዕብላ፣ አመ ትመጽእ በስብሐት ክርስቶስ ርእሰ መሐላ፣ ተውዐነ ለአግብርቲከ ውስተ ዐፀደ ፍግዕ ወተድላ፣ ናንሶሱ ምስሌከ በሐዳስ ቀጸላ::

ጌልጌላ ከምትባል ሰማይ ፀሐይ ፊት ለምታበራ ደመና በኋለኛው ሰዓት ለምትመጣበት ጊዜ ሰላምታ ይገባል:: በጌትነትህና በታላቅነትህ ክብር በመጣህ ጊዜ በልዩ ክብር አጊጠን ከአንተ ጋር እንመላለስ ዘንድ እኛን ባሮችህን ተድላ ደስታ ወዳለበት አደባባይ ጥራን::

እምሥራቀ ፀሐይ እስከነ ዐረብ ይትአኮት ስሙ ለእግዚአብሔር አምላክነ፣ ኪያከ ወልዶ ዘፈነወ ለነ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ ካህናቲነ፣ አስተጋብአነ ኀበ ትረፍቅ መካነ፣ እስመ ዝርዋን አግብርቲከ ንሕነ::

ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ የእግዚአብሔር ስሙ የተመሰነገ ይሁን ልጁን ወዳጁን አንተን ልኮልናልና:: ጠባቂያችን የካህናት አለቃ አንተ ነህ:: ስለዚህም አንተ ወዳለህበት ቦታ ሰብስበን እኛ ባሮች ተበታትነናልና::

ስብሐት ለከ አምላኪየ በኍልቈ ኵሉ ሥዕርትየ፣ ስብሐት ለከ አምላኪየ በኍልቈ ኵሉ አዕፅምትየ፣ ስብሐት ለከ አምላኪየ በኍልቈ ኵሉ ዘተርእየ፣ ስብሐት ለከ ንጉሥየ በኍልቈ ኵሉ ዘኢያስተርአየ፣ ስብሐተ ሥላሴከ ወትረ ይነግር አፉየ::

አምላኬ ሆይ በራስ ጸጉሬ ቁጥር ምስጋና ይገባሃል:: ፈጣሪዬ ሆይ በአንጥንቶቼ ቁጥር ምስጋና ይገባሃል:: ጌታዬ ሆይ በሚታየው ሁሉ ቁጥር ምስጋና ይገባሃል:: ንጉሤ ሆይ በማይታየውም ሁሉ ቁጥር ምስጋና ይገባሃል:: የሦስትነትህንም ምስጋና ሁል ጊዜ አፌ ይናገራል::

እምኵሉ ይኄይስ በሥላሴከ ተአምኖ፣ ወበወላዲትከ ተማኅፅኖ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እምቤተ መንግሥት ወተክህኖ፣ ተሰብእተከ እመቦ ዘያስተፈቅር መኒኖ፣ ያንኮርኩር ታሕተ ደይን ግዱፈ ከዊኖ::

ጌታዬ ኢየሱስ ሆይ ከሁሉ ይልቅ በሦስትነትህ መታመን ይበልጣል:: አንተን በወለደችም በማርያም መማፀን መልካም ዕድል ነው:: ፈጣሪዬ ክርስቶስ ሆይ ከቤተ መንግሥትና ከቤተ ክህነት ወገን የአንተን ሰው መሆን የሚጠራጠር ወይም አምላክ ሰው ሰው አምላከ መሆኑን የሚክድ ቢኖር ዕመቀ ዕመቃት መንጸፈ ደይን ወርዶ ይንከታከት::

ሰላም ሰላም በኵሎን መልክዕከ፣ አምሳለ መልክዑ ለአቡከ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕማማተ መስቀል ዘፆርከ፣ ኀብአኒ እምገጸ ሞት በእንተ ማርያም እምከ፣ አምላኪየ አምላኪየ ኢይጽናዕ ልብከ::

ጌታዬ ኢየሱስ ሆይ ከአባትህ መልክ ልዩነት ለሌለው መልክህ ደግሜ ደጋግሜ ሰላም እላለሁ:: ለእኛ ስትል አሥራ ሦትቱን ሕማማተ መስቀል ለተቀበልክ ላንተ ምስጋና ይገባል:: ፈጣሪዬ ክርስቶስ ሆይ ስለ እናትህ ስለ ማርያም ብለህ ከዓይነ ሞት ሠውረኝ:: አምላኬ አምላኬ ስልህ ልቡናህ አይጽናብኝ:: አዳኚዬ አምባ መጠጊያዬ አንተ ነህና::

አምላከ ምድር ወሰማያት አምላከ ባሕር ወቀላያት ወአምላከ ኵሉ ፍጥረት አምላኮሙ አንተ ለአበው ቀደምት አምላኮሙ ለነቢያት አምላኮሙ ለሐዋርያት አምላከ ጻድቃን ወሰማዕት መሐሪነ ለነ አምላክነ እስመ ግብረ እዴከ ንሕነ ወኢትዝክር ኵሎ አበሳነ::

የሰማይና የምድር አምላክ ሆይ የባሕርና የቀላያት አምላክ ሆይ የፍጥረቱ ሁሉ አምላክ ሆይ የቀደመ የአባቶቻችን አምላክ ሆይ የመላእክት አምላክ ሆይ የነቢያትና የሐዋርያት አምላካቸው ሆይ የጻድቃንና የሰማዕታት አምላክ ሆይ አቤቱ ሁላችንን ማረን የቅር በለን:: በደላችንንም አታስብብን:: በእጅህ ሥራዎች ነንና የእኔንም አገልጋይህን በደሌን ፋቅልኝ አጥፋልኝ አሜን::

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ዕቀበኒ ወድኅነኒ እመከራ ሥጋ ወነፍስ ሊተ ለ ________